# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

*በኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት የእህል ግዥ፣ ሽያጭ እና ክምችትን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት፡፡*

*ሐምሌ 2005.ዓ.ም.*

*አዲስ አበባ*

## Contents


**ክፍል አንድ** ........ 1

*መግቢያ* ........ 1

**የድርጅቱ አመሰራረት** ........ 1

**የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት ዓላማ፣** ........ 2

**የድርጅቱ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል** ........ 2

**የፋይናንስ ምንጭ** ........ 3

**የኦዲቱ ዓላማ** ........ 3

**የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ** ........ 4

**የኦዲት አካባቢ** ........ 4

**የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ** ........ 4

**የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች** ........ 5

የእህል ግዥና ሽያጭ ዕቅድ እንዲሁም የእህል ግዥ፣ ሽያጭ እና ክምችት የሥራ ሂደት መግለጫ ........ 6

በእህል ግዥና ሽያጭ  የእቅድ ዝግጅት የስራ ፍሰት ........ 6

የዋጋ አወሳሰን የስራ ፍሰት ........ 7

የእህል ግዥ ንዑስ የሥራ ሂደት የሚከናወኑ የግዥ አይነቶችና የስራ ሂደት መግለጫ ........ 7

የእህል ሽያጭ ንዑስ የሥራ ሂደት የሚከናወኑ የግዥ አይነቶችና የስራ ሂደት መግለጫ ........ 9

ክፍል ሁለት ........ 11

የኦዲት ግኝቶች ........ 11

2.1. ድርጅቱ የእህል ግዥ እና ሽያጭ አፈጻጸምን በየበጀት ዓመቱ የእቅድ መርሃ ግብር መሰረት ማከናወኑን በተመለከተ ........ 11

ድርጅቱ በጥናት ላይ የተመሰረተ የእህል ግዥ ዕቅድ የሚያዘጋጅና ተግባራዊ የሚያደርግ መሆኑን በተመለከተ ........ 11

በድርጅቱ የሚጠኑ ጥናቶች ተግባራዊ መደረጋቸውን በተመለከተ ........ 12

ድርጅቱ በውጭ አገርም ሆነ በአገር ውስጥ ያለውን የገበያ ድርሻ ማሳደጉን በተመለከተ ........ 13

የግዥ አፈጻጸም ክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ ........ 14

**2.2 ድርጅቱ የሚገዛቸው እና የሚያከማቻቸው እህሎች በድርጅቱ በተዘጋጀው የእህል ጥራት ቁጥጥር ክብካቤ እና ክምችት አስተዳደር መመሪያ  መሰረት ተግባራዊ  መሆኑን፣  እንዲሁም ድርጅቱ በበቂ የእህል ጥራት ቁጥጥር መሳሪያዎች የተደራጀ መሆኑን በተመለከተ፤** ........ 15

**በመጋዘኖች የሚቀመጡት እህሎች ድርጅቱ ባስቀመጠው የእህል ጥራትና ደረጃ መሰረት መሆኑን በተመለከተ፣** ........ 15

ለእህል ጥራት ማረጋገጪያ የሚውሉ የድርጅቱ መሳሪያዎችን በተመለከተ ........ 17

የእህል ጥራት ቁጥጥርና ክምችት ክብካቤ የአፈጻጸም መመሪያ በየጊዜው መከለሱን በተመለከተ፣ ........ 19
2.3 የድርጅቱ ወቅታዊ የእህል መረጃን ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ጋር ዘመናዊ በሆነ መልኩ የሚለዋወጥበት እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ግንኙነት የሚፈጥርበት ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፡፡ ........ 20
ወቅታቂ የእህል መረጃዎችን ዘመናዊ በሆነ መልኩ የሚለዋወጡበት ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ.. 20
ለድርጅቱ ሰራተኞች እና ባለድርሻ አካላት የሚሰጠውን ሥልጠና በተመለከተ ........ 21
ከአምራቾችና ከሸማቾች ማህበራት ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተ፣ ........ 22
2.4 የገበያ ማረጋጊያ ስንዴ እህል አቅርቦትና ስርጭትን በተመለከተ ........ 24
ክፍል ሦስት ........ 25
የመደምደሚያ ሃሳቦች ........ 25
ክፍል አራት ........ 27
የማሻሻያ ሃሳቦች ........ 27
አባሪ 1 ........ 29
የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ........ 29

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. በአንድ አገር ውስጥ ለፍጆታ የሚሆን የእህል ምርት ለተጠቃሚው የሚደርስበት የንግድ ሥርዓት ማበጀት አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ ሥርዓት መንግስት በሁሉም የአገሪቱ ክፍል ያለው ህብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ መሆኑን የሚያረጋግጥ መሆን አለበት፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የእህል ምርት በሚያጥረበት ጊዜም ሆነ ሰው ሰራሽ እጥረት ተፈጥሮ የእህል ዋጋ በሚንርበት ወቅት የገበያ ማረጋጋት ሚናውን መንግስት የመወጣት ግዴታ አለበት፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተጨማሪም አገሪቱ ምረትን ወደ ውጭ አገር በመላክ የውጭ ምንዛሪ የምታገኝበት መንገድም ሊመቻች ይገባል፡፡ ይህንን ተግባር እንዲወጡ ከተቋቋሙት ድርጅቶች መካከል የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት አንዱ ነው፡፡

## የድርጅቱ አመሰራረት

2. የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት በአዋጅ ቁጥር 113/1942 የኢትዮጵያ የእህል ቦርድ በመባል በ1942 ዓ.ም ተመሰርቶ እና በተለያዩ ስያሜዎች ሲጠራ ቆይቷል፡፡ በ1969 ዓ.ም የእርሻ ሰብል ገበያ ድርጅት የሚል ስያሜ ተሰጥቶት በአዋጅ ቁጥር 105/1969 ሲቋቋም በአገር ውስጥ ንግድ ሚኒስቴር ስር እንዲተዳደር የተደረገ ሲሆን በ1979 ዓ.ም የአገር ውስጥ ንግድ ሚኒስቴር ባወጣው ደንብ ቁጥር 103/1979 የእርሻ ሰብል ገበያ ኮርፖሬሽን በመባል ተሰይሟል፡፡ በኋላም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 104/1985 የመንግስት ልማት ድርጅት ሆኖ የኢትዮጵያ የእህል ንግድ ድርጅት በመባል እንደገና ተቋቁሞ ተጠሪነቱ ለመንግስት የልማት ድርጅት ተቆጣጣሪ ባለስልጣን እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በደንብ ቁጥር 58/1992 የኢትዮጵያ የቅባትና ጥራጥሬ ላኪ ኮርፖሬሽን ከድርጅቱ ጋር እንዲዋሃድ ተደርጓል፡፡ በመቀጠልም የአስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀት ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 380/96 መሰረት የድርጅቱ ተጠሪነት በቀጥታ ለግብርናና ገጠር ልማት ሚኒሰቴር እንዲሆን ተደርጓል፡፡ የፌዴራል አስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀትን፣ ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 ላይ የግብርና ምርት ግብይትን በሚመለከት ለግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት ለንግድ ሚኒስቴር ተላልፈዋል፡፡

## የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት ዓላማ፤

3. የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት በደንብ ቁጥር 58/1992 መሰረት የተቋቋመበት አላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

   1. የእህል ምርቶችን ከአገር ውስጥ አምራቾች በመግዛት ለሀገር ውስጥና በዋነኝነት ለውጭ ገበያ ማቅረብ፤
   2. የገበሬውን የእህል ማምረት ፍላጎት እንዲያድግ አስተማማኝ ገበያ የሚያገኝበት ሁኔታ እንዲፈጠር እገዛ ማድረግ
   3. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ስራዎችን መስራት

ናቸው፡፡

4. ከዚህም በተጨማሪ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ለድርጅቱ በተላለፈው ደንብ ቁጥር 104/1985 የድርጅቱ መብትና ግዴታዎች መሰረት ድርጅቱ ሸማቹ ህብረተሰብ በእህል ዋጋ ንረት እንዳይጎዳ ገበያን ማረጋጋት እና ለገበያ ማረጋጋት ተግባር የሚሆን መጠባበቂያ የእህል ክምችት መያዝ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡

5. ድርጅቱ በፊት ከሚያከናውነው የቅባት እና የጥራጥሬ እህሎች ንግድ በተጨማሪ ቡናን እንደ አንድና ዋንኛ የንግድ ዘርፍ እንዲሆን በመወሰን የቡና ንግድ ፍቃድ በማውጣት የቡና ግዥና ሽያጭ እንቅስቃሴውን ከመጋቢት ወር ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ በማከናወን ለአገሪቱ የውጭ ምንዛሬ በማፍራት ረገድ የበኩሉን ድርሻ እያበረከተ ይገኛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ድርጅቱ በአሁኑ ወቅት በከተሞች አካባቢ እየታየ ያለውን የኑሮ ውድነት ለማረጋጋት በመንግስት በተሰጠው ኃላፊነት መሰረት ከውጭ ሀገር ገበያ ስንዴን በመግዛት ለህብረተሰቡ፤ ለዳቦ ቤቶችና ለተለያዩ የምግብ አቅራቢ ድርጅቶች እያከፋፈለ ይገኛል፡፡

## የድርጅቱ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል

6. የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት 5 አባላት ባሉት የስራ አመራር ቦርድ፤ በአንድ ዋና ስራ አስኪያጅ፤ በአንድ ወሳኝ የስራ ሂደት (የእህል ግዥና ሽያጭ ወሳኝ የስራ ሂደት)፤ በስምንት ደጋፊ የስራ ሂደቶች፤ በአስር ቅርንጫፍ መ/ቤቶች እና በ63 የምርት መረከቢያ ጣቢያዎች ተዋቅሯል (አባሪ 1)፡፡ በዚህ አደረጃጀት የሚታቀፉ የሥራ መደቦችም በጥናቱ ተለይተው የተቀመጡ ሲሆን፤ በዚህም መሰረት በ2004 በጀት አመት መጨረሻ ላይ ድርጅቱ የነበረው የቋሚ ሰራተኞች ብዛት በትምህርት ደረጃ ሲታይ

ሁለተኛ ድግሪ 13 (1 በመቶ)፤ የመጀመሪያ ድግሪ 64 (5 በመቶ)፤ የኮሌጅ ዲፕሎማ 124 (10 በመቶ)፤ የልዩ ሞያ ዲፕሎማ 47 (4 በመቶ) እንዲሁም ከመሠረተ ትምህርት እስከ 12ኛ ክፍል ያጠናቀቁ 985 (80 በመቶ) ድርሻ አላቸው፡፡ በአጠቃለይ ድርጅቱ 439 ሴት እና 791 ወንድ በድምሩ 1230 ሠራተኞች አሉት፡፡

## የፋይናንስ ምንጭ

7. የእህል ንግድ ድርጅት እንደማንኛውም የልማታዊ ድርጅት በራሱ ገቢ የሚተዳደር ሲሆን፤ ይህም ለበጀት ዓመቱ የሚያስፈልገውን በጀት በራሱ አውጥቶ የስራ ማስኬጅያውን በጀት በሥራ አመራር ቦርድ ሲያጸድቅ፤ የካፒታልና የኢንቨስትመንት በጀት የሥራ አመራር ቦርድ ከገመገመው በኋላ የንግድ ሚኒስቴር (የቀድሞው የንግድና ኢንዱስትሪ ም/ቤት) እንዲያጸድቀው በማድረግ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

8. በዚህም መሰረት ከ 2002-2004 በጀት ዓመታት ያለው የድርጅቱ ገቢ፤ ወጪ እና ትርፍ እንደሚከተለው ቀርቧል

የሶስት በጀት ዓመታት የድርጅቱ ገቢ ወጪ እና ትርፍ በብር

| በጀት ዓመት | 2002 | 2003 | 2004 |
|---|---|---|---|
| ገቢ | 786,571,600.00 | 1,519,759,225.00 | 996,302,062.00 |
| ወጪ | 743,156,953.00 | 1,481,442,286.00 | 956,062,992.00 |
| ትርፍ | 43,414,647.00 | 38,316,839.00 | 40,239,070.00 |

## የኦዲቱ ዓላማ

9. የኦዲቱ ዓላማ በኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት እየተከናወነ ያለው የእህል ግዥ፣ ሽያጭ እና የክምችት ተግባር በቁጠባ እና በብቃት እየተከናወነ መሆኑን እና የገበያ ማረጋጋት ስራውም ውጤታማ እና የአምራቹን እና የሸማቹን ጥቅም ባስጠበቀ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን ለመገምገም ሲሆን ይህንን በተመለከተ የሚታዩ የአሠራር ድክመቶች ካሉ ድክመቶቹን እና መንስዔዎቻቸውን በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለማቅረብ ነው፡፡

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

10. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች /EGAS/ እና ለመስሪያ ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 669/2002 ዓ.ም በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ ኦዲቱ የሸፈነው ከ2002 እስከ 2004 በጀት ዓመታት የእህል ግዥ፤ሽያጭ፤ክምችት እና የገበያ ማረጋጋትን በተመለከተ የተከናወኑ ስራዎችን ነው፡፡ ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት ሲሆን ድርጅቱ በተለያዩ ክልሎች ካሉት 10 ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ውስጥ 5 ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን (የአዲስ አበባ ዙሪያ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፤የአሰላ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፤የናዝሬት ቅርንጫፍ ጽ/ቤትን፤ የባህር ዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤትን እንዲሁም የጅማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት) በናሙና መርጦ በማየት፤የተለያዩ መረጃዎችን በመከለስ፣ በአካል በመገኘት ያለውን የስራ ሁኔታና በስራቸው ባሉ መጋዘኖች ውስጥ ያለውን የእህል ክምችት እና ክብካቤ በተመለከተ የመስክ ጉብኝት በማድረግ፤ እንዲሁም ለተለያዩ ስራ ኃላፊዎች እና ባለድርሻ አካላቶች (የገበሬዎች ህብረት ስራ ማህበራት ፤የሸማቾች ህብረት ስራ ማህበራትን እንዲሁም የዳቦና ዱቄት ማምረቻ ፋብሪካዎችን) ቃለ መጠይቅ በማቅረብ ነው፡፡

## የኦዲት አካባቢ

11. የኦዲት ቡድኑ ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮችና ዘዴዎች መሠረት በማድረግ የኦዲት አካባቢ ለይቷል፡፡ ይኸውም፡-

> " በድርጅቱ እየተከናወነ ያለው የእህል ግዥ፣ ሽያጭ እና የክምችት ተግባር በቁጠባ እና በብቃት እየተከናወነ ስለመሆኑ እና የገበያ ማረጋጋት ስራውም ውጤታማ እና የአምራቹን እና የሸማቹን ጥቅም ባስጠበቀ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን መገምገም "፤

የሚል ነው፡፡

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ

12. ከላይ በተገለጸው የኦዲት አካባቢ ስር ሁለት የትኩረት አቅጣጫዎች እና ሶስት ንዑስ የኦዲት አቅጣጫዎች ተለይተዋል፡፡ እነርሱም፡-

1. የእህል ግዥ እና ሽያጭ ክንውን እንዲሁም የእህል ክምችትና አያያዝ በብቃት እና ኢኮኖሚያው በሆነ መልኩ መከናወኑን መገምገም፣

   1.1. የእህል ግዥ እቅድ አፈጻጸም በተቀመጠለት የጥራት፤መጠንና አይነት

መሰረት መከናወኑን መገምገም

1.2. የእህል ሽያጭ እቅድ አፈጻጸም በተቀመጠለት የጥራት፤መጠንና አይነት መሰረት መከናወኑን መገምገም፡፡

1.3. የእህል ክምችትና አያያዝ ስርዓቱ በብቃት፤በጥራት እና ኢኮነሚያው በሆነ መልኩ መከናወኑን መገምገም

2. የገበያ ማረጋጊያ ስንዴ እህል አቅርቦት በበቂ ጥናት በተደገፈ መልኩ መከናወኑን መገምገም የሚሉት ናቸው፡፡


## የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች

13. ከላይ የተመረጡትን ሁለት የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች እና ሶስት ንዑስ የኦዲት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚረዱ 15 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶቹም ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 1 ተያይዘዋል፡፡ በተዘጋጁት የመመዘኛ መስፈርቶቹም ላይ የድርጅቱ ኃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡


## የእህል ግዥና ሽያጭ ዕቅድ እንዲሁም የእህል ግዥ፣ ሽያጭ እና ክምችት የሥራ ሂደት መግለጫ

14. በእህል ግዥና ሽያጭ የስራ ሂደት ውስጥ የእህል እና ቡና ግዥም ሆነ ሽያጭ ከመከናወኑ በፊት የእቅድ ዝግጅትና የዋጋ አወሳሰን የስራ ፍሰት ያለ ሲሆን፤ በዚህ የስራ ፍሰት ውስጥ የሚከተሉት ተግባራት ይከናወናሉ፤

### በእህል ግዥና ሽያጭ  የእቅድ ዝግጅት የስራ ፍሰት



## የዋጋ አወሳሰን የስራ ፍሰት




## የእህል ግዥ ንዑስ የሥራ ሂደት የሚከናወኑ የግዥ አይነቶችና የስራ ሂደት መግለጫ

15. የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት እህል ግዥን በዋነኝነት በ6 አይነት መንገድ ማለትም በመደበኛ (ከመስክ እና መጋዘን ላይ ግዥ)፤ከምርት ገበያ(ለድርጅቱ እና በኮሚሽን ኤጀንትነት ለሌላ ድርጅት እህል መግዛት)፤ በወለል ዋጋ፣ በኮሚሽን መግዛት እና ከውጭ ሀገር የእህል ግዥ የሚያከናውን ነው፡፡

**የመደበኛ ግዥ፡-** በመደበኛ መግዛት አሰራር በመስክና በመጋዘን ላይ የሚከናወን ግዥን የያዘ ሲሆን፤ በመስክ ግዥ ከአምራቹ ከነጋዴ እና ከሌሎች እህል አቅራቢዎች እህሉ ባለበት ቦታ ከመጋዘን ውጭ ግገርው የሚፈጸም ሲሆን በመጋዘን ላይ ግዥ እህል አቅራቢው እምጥቶ በድርጅቱ መጋዘን የሚያስረክብበት የግዥ ስልት ነው፡፡

***ከምርት ገበያ መግዛት፡-*** በምርት ገበያ ማእከል የመጫረቻ መድረክ ላይ በመጫረት ለድርጅቱ ወይም በኮሚሽን ኤጀንትነት ለሌላ ድርጅት እህል የሚገዛበት የግዥ ስልት ነው፡፡

***በመጫረት መግዛት፡-*** የተለያዩ ድርጅቶች እህል ለመሸጥ በሚያወጡት ጨረታ ላይ በመሳተፍ የእህል ግዥ የሚካሄድበት አሰራር ነው፡፡

***በወለል ዋጋ መግዛት፡-*** በአርሶ አደሩ ከፍተኛ ምርት በሚመረትበትና የነጻ ገበያው ዋጋ ከአምራቹ የማምረቻ ዋጋ በሚያንስበት ወቅት አርሶ አደሩ ተጎጂ እንዳይሆን የሚካሄድ የእህል ግዥ ነው፡፡ በዚህም የግዥ ዘዴ ግዥ ከመከናወኑ በፊት ከድርጅቱ እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት በተውጣጡ ባለሙያዎች ጥናት በማከናወን ለመንግሰት የጥናት ሪፖርት ማቅረብ ውሳኔ እና የማካካሻ ጥያቄ ይቀርባል፡፡

***በኮሚሽን መግዛት፡-*** ድርጅቱ ባሉት የግዥ አውታሮች መድረስ በማይችሉበትና የእህል ፍሰቱ ተከታታይነት በሌለው ቦታዎች ግዥውን ለማጎልበትና አምራቹንም ለማበረታታት የእህል ግዥ በኮሚሽን ይከናወናል፡፡

***ከውጪ አገር መግዛት***፡- የእህል አቅርቦት የሸማቹንና የምግብ ፋብሪካዎች ፍላጎት ሊያሟላ ባልቻለበት ጊዜ አስፈላጊነቱ በመንግስት ሲወሰን እህል ከውጭ ኃገር ለመግዛት የሚያስችል ስልት ነው፡፡ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ ድርጅቱ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡፡ ከውጭ ሀገር እህል ለመግዛት የግብይትና የፋይናንስ ኦፊሰር፤ የጥራትና ክብካቤ፤ የትራንስፖርት እንዲሁም የእቅድና ገበያ ጥናት ባለሞያዎች በሀገሪቱ ውሰጥ የእህል አቅርቦቱ ከፍላጎቱ በታች መሆኑንና የመሸመቻ ዋጋ ከፍተኛ ስለመሆኑ በቅንጅት ጥናት ካጠኑ እና የበላይ የስራ አመራር በጥናቱ ሪፖርት ላይ ተወያይቶ ከወሰነ በኋላ ለመንግስት (ለስራ አመራር ቦርድና ለተቆጣጣሪ መስሪያ ቤት) የግዥ ሀሳብ አቅርቦ ያጸድቃል፡፡

የእህል ግዥ ጨረታ ማስታወቂያ በሀገር ውስጥና በውጪ እንዲተላለፍ በማድረግ የመንግስት ህግና ደንብን፤ ተከትሎ ግዥ በመፈጸም የተገዛውን እህል ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ ይደረጋል፡፡ ተገዝቶ መጋዘን የገባውን ንግድ ሚኒስቴር ባዘጋጀው የስንዴና የዳቦ የስርጭት አፈጻጸም መመሪያ መሰረት የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት በየክልሉ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎች ተመራጭ ለሆኑ የዱቄት ፋብሪካዎች፣ አከፋፋዮችና ጅምላ ነጋዴዎች እንዲሁም ዳቦ ቤቶች እንዲሸጥ በሚወስኑት የስንዴ መጠን ልክ እና በሚተመነው የስንዴ ዋጋ መሰረት የእጅ በእጅ ሽያጭ ይፈጽማል፡፡

## የእህል ሽያጭ ንዑስ የሥራ ሂደት የሚከናወኑ የግዥ አይነቶችና የስራ ሂደት መግለጫ

16. ድርጅቱ የእህል ሽያጭን በስድስት አይነት መንገዶች በመጫረት መሸጥ፣ በምርት ገበያ መሸጥ፣ የቅድሚያ ውል ሽያጭ፣ የእጅ በእጅ ጅምላ/ችርቻሮ ሽያጭ፣ የእጅ በእጅ የማረጋጋት ሽያጭ እና ውጭ አገር መሸጥ ይከናወናል፡፡

**በመጫረት መሸጥ** :-ከተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ላይ የጨረታ ማስታወቂያዎችን መከታተል፣ ጨረታው ሲገኝ የሰነድ መግዢያ መጠየቂያ ማዘጋጀት እና የጨረታ ሰነድ መግዛት፣ በጨረታው ላይ ለመሳተፍ በባለይ አካላት ፍቃድ ተሰጥቶ ሲገኝ ዋጋ ወስኖ ዋስትና በማስያዝ መሳተፍ፤ ድርጅቱ በጨረታው አሸናፊ ሆኖ ከተገኘ ከአጫራች ድርጅት ጋር ውል መዋዋልና የመልካም ስራ አፈጻጸም ማስያዝ፣ በጥራት መስፈርቱ መሰረት ለማደራጀትና ለማሸግ ናሙና መውሰድ፣ የተወሰደውን ናሙና በመከፋፈል የላቡራቶሪ ናሙና ማዘጋጀት፣ ናሙና ወስዶ ጥራቱን በማረጋገጥ እና በአግባቡ የተከማቸና የተጠበቀ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ በገዥው ተወካይ ጥራቱ ተመርምሮ እህሉን በማጓጓዝ መዝኖ በማስረከብ ገንዘብ የመሰብሰብ ተግባር ይከናወናል፡፡

**በምርት ገበያ መሸጥ**፡- የሚሸጠውን የእህል አይነት ወይም ቡና፣ የጥራት ደረጃና መጠን መወሰን፤ እህሉ ላለበት መጋዘን ትዕዛዝ መስጠት፣ እህሉን መዝኖ በሰነድ ወጪ ማድረግ፣ እህሉን ተረክቦ ማጓጓዝና ምርት ገበያ መጋዘን በማስረከብ የመረከቢያ ሰነድ መቀበል፣ የወቅቱን የገበያ ዋጋ በመገምገም መነሻና መድረሻ ዋጋ መወሰን የሚከናወን ሲሆን፣ በመጨረሻም ሳምንታዊ የሽያጭ ሪፖርት በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል በማቅረብ፣ የገንዘቡን ዝውውር መከታተልና ወደ ድርጅቱ አካውንት ገቢ መሆኑን ከተረጋገጠ በኋላ አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች በማጠናቀር እንዲያዙ ይደረጋል፡፡

**የቅድሚያ ውል ሽያጭ** :- የደንበኛውን ጥያቄ በመቀበል ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር ጥያቄው ከተገመገመ በኋላ ዋጋ የሚወሰን ሲሆን፣ ከዚያም በውሉ የጥራት መስፈርት መሰረት ናሙና መውሰድ፤ የተወሰደውን ናሙና በመከፋፈል የላቡራቶሪ ናሙና ማዘጋጀት፣ናሙና ወስዶ ጥራቱን በማረጋገጥ እና በአግባቡ የተከማቸና የተጠበቀ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ በገዥው ተወካይ ይመረመራል፡፡ በመቀጠልም የተደራጀውን እህል መዝኖ ደንበኛው በሰነድ ይረከባል፡፡

**የእጅ በእጅ ጅምላ/ችርቻሮ ሽያጭ**፡- ደርጅቱ በዚህ አይነት መንገድ የእህል መሸጥ ፍላጎት ሲኖረው በተወሰነው የመሸጫ ዋጋ መሰረት የእጅ በእጅ ሽያጭ ኢንቮይስ በማዘጋጀት ገንዘብ በመቀበልና የማስረከቢያ ሰነድ በማዘጋጀት መዝኖ በማስረከብ ይከናወናል፡፡

**የእጅ በእጅ የማረጋጋት ሽያጭ** ፡-የእህል አቅርቦትና ፍላጎት፣ የሸማቹን ሁኔታ እና በእጅ ላይ ያለውን ክምችት መጠንና ዋጋ በማወቅ ለማረጋጋት የሚያስፈልገውን ተጨማሪ የእህል መጠን፣ ዋጋ፣ ጥራትና የማሰራጫ ወጪ የማስላት ተግባር ይከናወናል፡፡ እህሉ የሚገኝበትን ምንጭ በመለየት ለተቆጣጣሪ መ/ቤትና ለስራ አመራር ቦርድ አቅርቦ ይወሰናል፡፡ በመቀጠልም ተጠቃሚውን ለይቶ በመመዝገብ፣ በተወሰነው የመሸጫ ዋጋ መሰረት የእጅ በእጅ ሽያጭ ኢንቮይስ በማዘጋጀት ሽያጩ ይከናወናል፡፡

**ውጭ አገር መሸጥ** ፡- ከደንበኛ ጋር ግንኙነት በመፍጠር በመደራደርና የሽያጭ ውል በመወሰን የመፈራረም ተግባር ይከናወናል፡፡ ከዚያም Letter of Creadit (L/C )በመክፈት የግብይት ሥርዓት መሠረት ሽያጩ ይከናወናል፡፡ ለውጪ ገበያ የሚቀርበው ምርት የግብርና ኳራንቲን የገኘ ተወካይ ሰርቬየርስና ጉምሩክ ፎርማሊቲ ማሟላት ይጠበቅበታል፡፡

# ክፍል ሁለት

# የኦዲት ግኝቶች

## 2.1. ድርጅቱ የእህል ግዥ እና ሽያጭ አፈጻጸምን በየበጀት ዓመቱ የእቅድ መርሃ ግብር መሰረት ማከናወኑን በተመለከተ

### ድርጅቱ በጥናት ላይ የተመሰረተ የእህል ግዥ ዕቅድ የሚያዘጋጅና ተግባራዊ የሚያደርግ መሆኑን በተመለከተ

17. የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት በጥናት ላይ የተመሰረተ ዓመታዊ የእህል ግዥ ዕቅድ በማዘጋጀት በዋናው መ/ቤት እና በሥሩ ባሉ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡

18. በኦዲቱ ወቅት ከድርጅቱ በተገኘው የእቅድ ክንውን መረጃ መሰረት ከ2002-2004 ባሉት የበጀት ዓመታት የድርጅቱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚያከናውኑት የእህል ግዥ ከዕቅዱ አንጻር ዝቅተኛ መሆኑ ታውቋል፡፡ በዚህም መሰረት ድርጅቱ ባሉት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አማካኝነት በ 2002 በጀት ዓመት 1,495,000 ኩንታል የተለያዩ የእህል አይነቶችን ለመግዛት አቅዶ 458,095 ኩንታል እህል (ይህም የእቅዱን 31%)፣ በ2003 በጀት ዓመት 1,634 000 ኩንታል የተለያዩ የእህል አይነቶች ለመግዛት አቅዶ 877,959 ኩንታል (የእቅዱ 54 %)፣ እንዲሁም በ2004 በጀት ዓመት 1,752,000 ኩንታል እህል ለመግዛት አቅዶ 781,227 ኩንታል (የእቅዱን 45 %) ማከናወኑ ታውቋል፡፡

19. በተጨማሪም በኦዲት ወቅት በናሙና ከተመረጡት(ናዝሬት፤አሰላ፤ባህር ዳር እና ጅማ) የድርጅቱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከተሰበሰበው መረጃ ለመረዳት እንደተቻለው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ የየበጀት ዓመቱን እቅድ ሲያዘጋጁ ከየወረዳው/ ክልል የግብርና ጽ/ቤቶች/ ቢሮዎች የምርት ግምገማ መረጃን ወጥነት ባለውና ታአማኒነት ባለው መልኩ እንደማይሰበስቡ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

20. በዚህ ጉዳይ ላይ የየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የየበጀት ዓመቱን የምርት ግምገማ መረጃን በቃል ከወረዳ ግብርና ጣቢያ ሃላፊዎች እንደሚሰበስቡ ገልጸው ወጥነት ባለው መልኩ በመረጃ አስደግፈው የመሰብሰብ ስራ እንብዛም እንደሌለ ገልጸዋል፡፡

21. ስለሁኔታው የድርጅቱ የእህል ግዥና ሽያጭ ወሳኝ የስራ ሂደት ስራ አስኪያጅ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ድርጅቱ ከተሰጠው ዓላማ አንጻር ማንኛውንም ግዥ

ሲያከናውን አምራቹ ማግኘት የሚገባውን ዋጋ በመመርኮዝ እንዲሁም የገበያውን ዋጋ የማያንር ከሆነ ግዥ እንደሚፈጽም የገበያ ዋጋ አናሳ ነው ተብሎ ወደ ግዥ እንደማይገባ ገበያን ለማረጋጋት ተብሎ ከግዥ የሚቆጠቡበት ጊዜ መኖሩን፣ ሽያጭም ሲያከናውኑ በአብዛኛው ለመንግስት ተቋማት፣ ለእርዳት ሰጪ ድርጅቶች፣ለአለም አቀፍ የምግብ ተቋም መሆኑን፣ በተጨማሪም ለማንና ለምን እንደሆነ ተጣርቶ ነው ሽያጭ የሚያከናውኑ መሆኑን፣ ይህን ችግር ለመቅረፍ አዳዲስ ገበያ በመክፈትና ወደ አምራቹ በመቅረብ ግዥ የማከናወን ስራ እየሰሩ እንደሚገኙ ገልጸዋል፡፡

22. ድርጅቱ በየበጀት ዓመቱ ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እንደግብዓት እየተጠቀመ የእህል ግዥ እቅዱን የሚያዘጋጅበት የምርት ግምገማ መረጃን ተአማኒነት ባለው መልኩ እና በመረጃ በተደገፈ ሁኔታ አለመጠቀሙ በበቂ ጥናትና መረጃ ላይ ያልተመሰረተ ዕቅድ እንዲይዝ እና ዕቅድ ክንውኑ አነስተኛ እንዲሆን አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

**በድርጅቱ የሚጠኑ ጥናቶች ተግባራዊ መደረጋቸውን በተመለከተ**

23. ድርጅቱ የተቋቋመበትን አላማ ለማሳካት እና በመስኩ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመገኘት እንዲረዳው የተለያዩ ጥናቶችን በማስጠናት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ድርጅቱ ባጠናውና ተግባራዊ እያደረገ ባለው የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት መሰረት የእህል ዋጋ የመወሰን ስልጣንን ከማእከል አሰራር ወደ ስራው ባለቤቶች የማውረድ ስራን ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

24. በኦዲቱ ወቅት ድርጅቱ መሠረታዊ አሰራር ሂደት ለውጥ ጥናት አካሂዶ ተግባራዊ ማድረግ መጀመሩ ታውቋል፡፡ በዚህም መሠረት በጥናቱ የተካተተው በማዕከል ብቻ ተወስኖ የነበረውን የእህል ዋጋ የመወሰንን ሥልጣን ወደ ስራ ባለቤቶቹ እና ወደ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ማውረድ እንዳለበት ተቀምጧል፡፡ ሆኖም በእህል ግዥ ላይ የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊው በተወሰነ መልኩ ዋጋ የመወሰን ኃላፊነት እንዲሰጠውና እንዲወሰን የተጠናው ጥናት ላይ ቢቀመጥም ተግባራዊ እንዳልተደረገና የእህል ግዥ ዋጋ አወሳሰን ሥርዓት በማዕከል ብቻ በዋናው መ/ቤት እንደተያዘ ታውቋል፡፡ የእህል ግዥ ፍቃድ ተሰጥቷቸው ወደ ገበያ ሲገቡ ያለው የገበያ ዋጋ ተለዋዋጭ በመሆኑ የተነሳ እና ምንም የመንሸራሸሪያ ዋጋ ስላልተሰጣቸው ገበያ ላይ ወጥተው ምንም ግዥ ሳያከናውኑ የሚቀርበት ሁኔታ እንደሚፈጥርባቸው የአዲስ አበባ እና የባህር ዳር ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች የስራ ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

25. በዚህ ጉዳይ ላይ የድርጅቱ የእህል ግዥና ሽያጭ ወሳኝ የስራ ሂደት ባለቤት ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ዋጋ የመወሰን ስልጣን በዋናው ስራ እስኪያጅ የተወሰነ ነው፡፡ ሆኖም

አሁን ባለው የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የአቅም ውስንነት ማለትም በሀገር አቅፍ ደረጃ ያለውን የገበያ ሁኔታና በድርጅት ደረጃ ባለው የዓቅም ውስንነት ይህን የእህል ዋጋ የመወሰን ስልጣን ቢሰጣቸው ለማስፈጻም እንደሚከብድ ገልጸዋል፡፡ ሆኖም ግን የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ኃላፊዎችን የሀገር አቀፍ የገበያ ሁኔታን የሚያውቁበትን መንገድ በማመቻቸት እና አቅማቸውን በማዳበር ይህ ኃላፊነት እንደሚሰጣቸው እና አሁንም በሚያቀርቡት የውሳኔ ኃሳብ በጋራ ውይይት በመወሰን ላይ እንደሚገኙ ገልጸዋል፡፡ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ በመውጫ ስብሰባ ወቅት ደግሞ ዋጋ በተጠየቀ በ30 ደቂቃ ውስጥ መወሰን እንዳለበት እንጂ ለሥራ ሂደቶች ወይም ለቅርንጫፎች በውክልና ይሰጥ የሚለው ጉዳይ በጥናቱ አልተካተተም ብለዋል፡፡ የዋጋ ውክልና ለሥራ ሂደት ባለቤቶች ይሰጥ የሚለው በጥናቱ ላይ በግልጽ በመቀመጡ የተሰጠውን መላሽ አልተቀበልነውም፡፡

26. ይህም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በእህል ግዥ ወቅት በጊዜ ወደ ገበያ ገብተው እህል እንዳይገዙ ሊያደርጋቸው፤ ግዥ አግኘተውም ዋናው መ/ቤት እስከሚፈቅድላቸው ድረስ የገበያ ዋጋ ስለሚቀያየር ግዥ መጀመሪያ በነበረው ዋጋ እንዳይፈጽም ያደርጋል፡፡

**ድርጅቱ በውጭ አገርም ሆነ በአገር ውስጥ ያለውን የገበያ ድርሻ ማሳደጉን በተመለከተ**

27. ድርጅቱ በገበያ ውስጥ የሚሳተፍባቸው የእህል ግዢና ሽያጭ አይነቶች በማሳደግ በሀገር አቀፍ ደረጃ ያለውን የገበያ ድርሻ ሊያሻሽል ይገባል፡፡ በተጨማሪም ከተቋቋመበት ዓላማ አንዱ የሆነውን የእህል ምርትን በዋነኛነት ለአለም አቀፍ ገበያ ማቅረብ የሚለውን ለማሳካት ወደ ውጭ የሚልካቸውን የእህል ምርቶች መጠን ና ዓይነት ሊያሳድግ ይገባል፡፡

28. ድርጅቱ በመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናቱ ላይ የገበያ ማስፋፊያ እና አማራጭ የኤክስፖርት ገበያዎችን እንደሚያስፋፋ ቢገልጽም የመሰረታዊ የስራ ሂደት ጥናቱ ተግባራዊ ከመደረጉ በፊትም ሆነ በኋላ በ16 የምርት አይነቶች የእህል ግዥና ሽያጭ ስራ ውስጥ እንደሚገኝ ታውቋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በመሰረታዊ የስራ ሂድት ለውጥ ጥናቱ ላይ አስፈላጊው የገበያ ጥናትና ልማት ስራ በማከናወን ወደ አዳዲስ ገበያ በመግባትና ተጨማሪና አማራጭ የኤክስፖርት ገበያዎችን እንደሚፈጥር አስቀምጦ፤ በዚህም ድርጅቱ ያለውን የውጭ ገበያ ድርሻ ከ 3 ከመቶ ወደ 6 ከመቶ የማሳደግ በጥረት ተደራሽ ግብ ይዟል፡፡ከድርጅቱ ከቀረቡ መረጃዎችም ሆነ ከብሄራዊ ባንክ ከተገኘው መረጃ ለመረዳት እንደተቻለው በወጪ ንግድ ሽያጭ የድርጅቱ አገር አቀፍ የገበያ ድርሻ በ2002 በጀት ዓመት 4.48 ከመቶ ፤በ2003 በጀት ዓመት 6.46 ከመቶ እንዲሁም በ2004 በጀት ዓመት 2.47 በመቶ መሆኑ ታይቷል፡፡

29. ድርጅቱ ባለፉት 3 ዓመታት ተግባራዊ እያደረገ ባለው አዲሱ የመሰረታዊ የስራ ሂደት

ለውጥ ጥናት ላይ ድርጅቱ ያቀደውን ያህል እህል ላለመግዛቱና የግዥ መጠኑን ማሳደግ ካልቻለባቸው ምክንያቶች መካከል ፈቃድ የሌላቸው የእህል ነጋዴዎች በብዛት ገበያ ውስጥ መግባታቸውና የገበያ ሽሚያ መፍጠራቸው እንደሆነ በማስቀመጥ ይህንን ችግር ለመቅረፍ ከምርት ገበያ ድርጅት ጋር በበለጠ በመስራት ህጋዊነትን ማጠናከር የሚል የመፍትሄ ሀሳብ በማቅረብ ያስቀመጠ ቢሆንም ባለፉት 3 ዓመታት በዚህ ጉዳይ ድርጅቱ ለሚመለከታቸው አካላት ስለጉዳዩ ጠለቅ ያለ አውደ ጥናት በማዘጋጀትም ሆነ በሌላ መልኩ ችግሩን ለመፍታት ያደረገው ጥረት አለመኖሩ ታውቋል፡፡

30. ስለጉዳይ የድርጅቱ የእህል ግዥና ሽያጭ ወሳኝ የስራ ሂደት ባለቤት ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ደንበኛን መሰረት ባደረገ መልኩ የእህል ግዥን የሚያከናውኑ መሆኑን፤ ሆኖም የገበያ አድማሳቸውን ለማስፋት ችግር የሆነባቸው መሆኑን፣ ለምሳሌ ደንበኞች የሚፈልጉትን የእህል ጥራት አይነት ከገበያው የማያገኙበት ሁኔታ ሲፈጠር የእህል ግዥን የማይፈጽሙበት ጊዜ መኖሩን፣ የአለም አቀፍ የገበያ ድርሻ ያነሰበት በዋጋ አለመስማማት ምክንያት መሆኑን፣ ይኸም ከውጭ ካለው የእህል ተቀባይ ጋር በማይስማሙበት ወቅት ሽያጫቸው በዚያው መጠን የሚያንስ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በውጭ ንግድ ዘርፍ እንቅስቃሴያቸው በንግድ ባንክ በየአመቱ ተሸላሚ መሆናቸውን በመውጫ ስብሰባ ወቅት ኃላፊዎቹ ገልጸዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ ድርጅቱ ካስቀመጠው እቅድ በታች ክንውን በመፈጸሙ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

31. ድርጅቱ በእቅዱ መሰረት የሚገበያቸውን የእህል አይነቶች አለማሳደጉ የድርጅቱ የዓለም አቀፍም ሆነ የአገር ውስጥ የገበያ ድርሻ አናሳ እንዲሆን አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

### የግዥ አፈጻጸም ክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ

32. በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ግዥ፤ ሲከናወን የአፈጻጸም ስርዓቱን ሊያጠናክር የሚችል የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ የሚዘረጋው ሥርዓትም ዋናው መ/ቤት ለቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች፣ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ደግሞ ለግዥ ማዕከላት የሚያስተላልፉት ገንዘብ ለተባለለት አላማ በተባለበት ጊዜ መዋሉን ማረጋገጥ የሚያስችል መሆን አለበት፡፡

33. በኦዲቱ ወቅት በአዲስ አበባ ዙሪያ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ካገኘነው መረጃ እንደተረዳነው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ለግብይት እና ክምችት ሰራተኞች በቀጥታ በስማቸው የእህል ግዥ እንዲያከናውኑ በባንክ ገንዘብ የሚልክ ሲሆን ይህም ገንዘብ በስርዓቱ እና በወቅቱ ለሚፈለግበት ተግባር መዋሉን ማእከሉ እህሉን ገዝቶ ማስገባቱን የሚቆጣጠርበት የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ አልተገኘም፡፡

34. ስለጉዳይ የድርጅቱ የእህል ግዥና ሽያጭ ወሳኝ የስራ ሂድት ባለቤት ተጠይቆ በሰጡት መልስ ይህን የሚያመላክት መጥፎ አጋጣሚ ውይም ልምድ እንዳላጋጠማቸው ሆኖም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ይህንን የስራ አፈጻጸም የመቆጣጠር የስራ ኃላፊነት አለባቸው በማለት ገልጸዋል፡፡

35. ለእህል ግብይት ለግዥ ማዕከላት በግለሰቦች ስም በባንክ የሚላከው ገንዘብ በተባለለት ጊዜ ለተባለለት አላማ መዋሉን ለማረጋገጥ የሚያስችል የቁጥጥር ሥርዓት አለመዘርጋቱ የመንግስት ገንዘብን አላግባብ እንዲባክን በር ሊከፍት ይችላል፡፡፡

## 2.2 ድርጅቱ የሚገዛቸው እና የሚያከማቻቸው እህሎች በድርጅቱ በተዘጋጀው የእህል ጥራት ቁጥጥር ክብካቤ እና ክምችት አስተዳደር መመሪያ መሰረት ተግባራዊ መሆኑን፣ እንዲሁም ድርጅቱ በበቂ የእህል ጥራት ቁጥጥር መሳሪያዎች የተደራጀ መሆኑን በተመለከተ፤

**በመጋዘኖች የሚቀመጡት እህሎች ድርጅቱ ባስቀመጠው የእህል ጥራትና ደረጃ መሰረት መሆኑን በተመለከተ፣**

36. የድርጅቱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እህል ሲገዙም ሆነ ሲያከማቹ ድርጅቱ ባስቀመጠው የጥራት ደረጃ መመሪያ መሰረት ሊሆን ይገባል፡፡ ይህም የእህሎች የጆንያ አስተሻሸግ፣ በመጋዘን ውስጥ አደራደር፣ የመጋዘኖች መለያ ኮድ አለባጠፍን ሊጨምር ይገባል፡፡ በተጨማሪም ድርጅቱ ለእህል ማከማቻ የሚጠቀምባቸው መጋዘኖች የድንገተኛ እሳት ማጥፊያ መሣሪያ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

37. የድርጅቱ የእህል ጥራት ቁጥጥር እና ክብካቤ አፈጻጸም መመሪያ ላይ እንደሚያዘው በመጋዘኖች ውስጥ ያለው የእህል አያያዝ እና አደራደር ለእህል ተባይ መከላከል ተግባር አስፈላጊ መሆኑን የሚገልጽ ቢሆንም በኦዲት ወቅት በናሙና ከታዩት 3 በናዝሬት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥር የሚገኙ የእህል መጋዘኖች የእህል አደራደር የተዝረከረከ እና የተዘበራረቀ መሆን፤ በመጋዘኖቹ ወስጥ እህል ከመቋጠሪያ ፊሶ መታየቱ፣ በተጨማሪም በመጋዘኖቹ ውስጥ እህል ያልተያዘባቸው የእህል መቋጠሪያ ጆንያዎች በብዛት ተከማችተው እና ተዝረክርከው መገኘታቸው፣ የድንገተኛ የእሳት ቃጠሎ ለመከላከል የሚያስችል የእሳት ማጥፊያ መሣሪዎች አለመኖሩ፣ በመጋዘኖቹ ላይ የመጋዘን መለያ ኮድ ያልተለጠፈባቸው መሆን፣ በየመጋዘኖቹ የእህል ማስቀመጫ ፓኔሎች የሌሉ በመሆኑ እህል መሬት ላይ እንዲቀመጥ መደረጉ፣ በመጋዘን ቁጥር 11 ግቢ ውስጥ ግለሰቦች ኑሮ መስርተው እየኖሩ መሆኑን፣ በመጋዘኑ ውስጥ አእዋፋት የሚገቡበት ሁኔታ እንዳለ እንዲሁም አገልግሎት የማይሰጡ እና የተበላሹ ብዛት ያላቸው የእህል ማበጠሪያ ማሽኖች

በየመጋዘኖቹ ተተክለው መገኘታቸውን ለመመልከት ተችሏል፡፡

38. በሌሎች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች (አሰላ፣ ጅማ፣ ባህርዳር) የኦዲት ቡድኑ ለምልከታ በሄደበት ወቅት እህል በመጋዘኖች ውስጥ አልነበረም፡፡ የአሰላንና የባህር ዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መጋዘን ውስጥ ለእህል ህክምና አገልግሎት የሚውሉ መድኃኒቶች አያያዝ የተዝረከረከ እና መድኃኒቶቹ በሰው እና በአካባቢ ላይ አደጋ ሊያስከትሉ በሚችሉበት ሁኔታ እንደተቀመጡ ለመመልከት ተችሏል፡፡



ፎቶ 1፡ በአዳማ በመጋዘኖች ውስጥ የተለያዩ አእዋፋት የሚታዩበት ሁኔታ መኖሩን የሚያሳይ ምስል



ፎቶ 2፡ አገልግሎት የማይሰጡ የእህል ማበጠሪያ ማሽኖች በእህል ማከማቻ መጋዘኖች ውስጥ ተቀምጠው የሚታዩበት ምስል

39. ስለጉዳዩ የየቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የስራ ባለሞያዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ይህ በመሆኑ እስከአሁን ድረስ ምንም አይነት ችግር ባለማጋጠሙ ለመድኃኒቶቹ ማስቀመጪያ የሚሆን መደርደሪያ አለመሰራቱን ገልጸው ሆኖም ግን መደርደሪያ ቢሰራ ጠቃሚ እንደሆነ በቃል አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡



ፎቶ3 ፡በናዝሬት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ስር በሚገኝ መጋዘን ውስጥ እህል ያልያዙ ጆንያዎች አቀማመጥ ሁኔታ የሚያሳይ ምስል



ፎቶ 4፡በናዝሬት ቅርንጫፍ መጋዘን ቁጥር 11 ውስጥ የግለሰቦች የሚኖሩበት መኖሪያዎች በከፊል የሚያሳይ ምስል

40. ይህንንም በተመለከተ የድርጅቱ ኃላፊዎች ተጠያቀው በሰጡት መልስ፤ አንዳንድ መጋዘኖችን ድርጅቱ ሲረከባችው መጋዘኖቹ ከነበረባቸው ጉድለት ጋር በመሆኑ በአንዳንድ መጋዘኖች አካባቢ ሰው ሊኖርባቸው እንደሚችል ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ባሉት መጋዘኖች ከፍተኛ የስራ ፍሰት በተደጋጋሚ ያለ በመሆኑ ይህ የእህል ጥራት ክብካቤ አፈጻጸም መመሪያን ጠብቆ አለመስራት ሁኔታ እንደሚያጋጥም፣ እህል ከተሞላበት ጆንያ የደንበኞቻችን ስም ወዳለበት ማሽጊያ ሲገለባበጥና ሲበጠር የሚፈስበት ሁኔታ መኖሩ፣ ሆኖም ይህ ሁኔታን ለመግታት ከፍተኛ ክትትልና ጥንቃቄ እና በክምችቱ አስፈላጊው እንክብካቤ እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ ድርጅቱ መጋዘኖቹን ከተረከበ ረጅም አመታት ያስቆጠሩ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

41. ይህም በመሆኑ ድርጅቱ የሚያከማቸው እህል ለብልሽትና ለብክነት ከማጋለጡም በላይ መጋዘኖቹ ደረጃቸውን የጠበቁ አለመሆን ድርጅቱ ለዓለም ገበያ በሚያቀርበው እህል ላይ ጥራት በመቀነስ በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዳይሆን ሊያደርገው ይችላል፡፡

**ለእህል ጥራት ማረጋገጪያ የሚውሉ የድርጅቱ መሳሪያዎችን በተመለከተ**

42. ድርጅቱ የሚገዛቸውን እህሎች አስፈላጊውን ጥራት ያሟሉ መሆናቸውን በመጀመሪያ

ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ ይህንንም ለማድረግ እንዲያስችለው ለእህል ጥራት ማረጋገጪያ የሚውሉ መሳሪያዎች ዘመናዊና በበቂ መልኩ እና በሚፈለግበት የስራ ቦታዎች ሊያሟላ ይገባል፡፡

43. በድርጅቱ የ2000-2004 በጀት ዓመታት እስትራቴጂክ እቅድ ላይ እንደ ግብ ከተቀመጠው ነጥብ አንዱ ያረጁ የእህል ጥራትና ደረጃ መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች በዘመናዊ መሳሪያዎች የሚተኩበት ዝርዝር ጥናት በማድረግ ከ2001 ጀምሮ እስከ 2004 ድረስ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ማድረግ የሚል እቅድ ይዞ ነበር፡፡ ሆኖም በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት ናዝሬት፣ አሰላ፣ ባህር ዳር፣ ጅማ እና አዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ውስጥ የእህል ጥራት ማረጋገጪያ መሳሪያዎች በተለይም ዘመናዊ የእህል እርጥበት መለኪያ እና የናሙና መለኪያ ሚዛን በዕቅዱ መሰረት ተገዝተው ለየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና ግኘ ማእከላት አለመሰራጨታቸው ታውቋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በናዝሬት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥር በሚገኙት የእህል መጋዘኖች ውስጥ ያሉት የእህል ማበጠሪያ ማሽኖች እብዛኛዎቹ ያረጁና አገልግሎት እንደማይሰጡ ለመረዳት ተችሏል፡፡

44. በዚህ ጉዳይ የድርጅቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የኢትዮጵያ የምርት ገበያ ድርጅት ECX በሚገኝባቸው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በሙሉ ይህ ዘመናዊ መሳሪያ ይኖራል የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ የእህል ጥራት ማረጋገጪያ መሳሪያዎችን ለመግዛት በዕቅድ ይዘን የነበረ ሲሆን መሳሪያዎቹን በዕርዳታ ስላገኘናቸው አልገዛንም፡፡ አሁን ያለብን ችግር የእህል ጥራት ሸራ ነው ይህንንም የአለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ (International Fund for Agricultural Development, IFAD) እንደሚገዛልን ቃል ገብቶልን የነበረ ቢሆንም ግኘው በመዟተቱ ችግሩን ለመቅረፍ በዘንድሮ በጀት ዓመት በራሳችን በጀት 100 ሸራ ለመግዛት እቅድ ይዘናል አገልግሎት የማይሰጡ ማበጠሪያዎችን በተመለከተ መለዋወጫ ከአንደኛው እየወሰድን ሌሎች ማበጠሪያዎችን ለማንቀሳቀስ እየተጠቀምንበት ሲሆን በመቀጠል ግን ያሉበት ሁኔታን በደንብ ጥናት ተደርጎ ለወደፊቱ አገልግሎት የማይሰጡ በመንግስት መመሪያ መሰረት የሚወገዱበት ሁኔታ እንደሚመቻች በመውጫ ስብሰባ ወቅት ገልጸዋል፡፡ ይህን ይበሉ እንጂ በዕርዳታ ተገኙ የተባሉት መሣሪያዎችም በድርጅቱ ዕቅድ መሰረት በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ባለመገኘታቸው የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡



ፎቶ 5፡ በባህር ዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ውስጥ የሚገኘው ዘመናዊ ያልሆነው የእህል እርጥበት መለኪያ (ሴራ ቴስተር)

**የእህል ጥራት ቁጥጥርና ክምችት ክብካቤ የአፈጻጸም መመሪያ በየጊዜው መከለሱን በተመለከተ፣**

45. ድርጅቱ የሚጠቀምበት የእህል ጥራት ቁጥጥርና ክምችት ክብካቤ የአፈጻጸም መመሪያ በየጊዜው ሊከለስና ወቅታዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ መመሪያው ሲከለስም በየጊዜው የሚቀያየረውን የድርጅቱ አደረጃጀትና የእህል ክብካቤ ሁኔታ ጋር በተጣጣመ መልኩ መሆን አለበት፡፡ ከዚሁ ጋር አብሮ ከመመሪያው ጋር ተያያዥነት ያላቸው መመሪያዎችና ደንቦችም አብረው ሊከለሱ ይገባል፡፡

46. የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት አሁን እየሰራበት ያለው የእህል ጥራት ቁጥጥርና ክምችት ክብካቤ የአፈጻጸም መመሪያ የተዘጋጀው በ1986 ዓ.ም ሲሆን በአሁኑ ወቅት ካለው ተለዋዋጭ የገበያ ሁኔታ ጋር እና የድርጅቱ የመሰረታዊ የስራ ሂደት ጥናት ጋር በተጣጣመ መልኩ ተከልሶ ወቅታዊ አልተደረገም፡፡ በተጨማሪም በናሙና ከተመለከትናቸው የድርጅቱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች (በአሰላ፣ጅማ፣በባህር ዳር) የእህል ጥራት ቁጥጥርና ክብካቤ የአፈጻጸም መመሪያ አልተገኘም፡፡

47. ስለጉዳዩ የየቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ መመሪያውን ተረክበው የነበሩት የስራ ኃላፊዎች በተለያየ ምክንያት መስሪያ ቤቱን ለቀው በመሄዳቸው መመሪያው ሊገኝ አለመቻሉን ገልጸዋል፡፡

48. ይህንንም በተመለከተ የድርጅቱ ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ መመሪያዎቹ እና ደንቦቹ ለመከለስ ቢዘገዩም ከመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት በኋላ የተወሰኑ መመሪያዎች ተከልሰው ስራ ላይ የዋሉ  መኖራቸውን እንዲሁም ለመከለስ በሂደት ላይ ያሉ መመሪያዎች መኖራቸውን ገልጸዋል፡፡ በቅርንጫፍ መ/ቤቶቹ መመሪያዎቹ አለመገኘቱን በሚመለከት ደግሞ ድርጅቱ ለእያንዳንዱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መመሪያው ልኮ ለዓመታት ሲሰሩበት መቆየታቸውን አሁንም እየሰሩበት መሆኑን እንደሚያውቁ፣ እንደ አስፈጻሚ አካል መመሪያዎቹ እነሱ ጋር ሊኖር እንደሚገባ የለም ካሉ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ይህን ጉዳይ ሊያርሙ ይገባል በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

49. መመሪያው በሁሉም ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ስለመኖሩ ዋናው መስሪያ ቤት ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ከዚህም ባሻገር መመሪያው በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ አለመኖሩ ሁሉም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በመሰላቸው እና በልምድ እንዲሰሩ በር ከመክፈቱም በላይ በብዙ ወጪ የተገዙ እህሎች ጥራት ቁጥጥር እና ክምችትበአግባቡ እንዳይከናወን ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 2.3 የድርጅቱ ወቅታዊ የእህል መረጃን ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ጋር ዘመናዊ በሆነ መልኩ የሚለዋወጥበት እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ግንኙነት የሚፈጥርበት ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፡፡

### ወቅታቂ የእህል መረጃዎችን ዘመናዊ በሆነ መልኩ የሚለዋወጡበት ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ

50. ድርጅቱ ወቅታዊ የሆኑ የእህል የገበያ ዋጋና ተዛማጅ መረጃዎችን አጠናቅሮ ሊይዝ ይገባል፡፡ እነዚህንም መረጃዎች ዘመናዊ በሆነ የመለዋወጫ ዘዴ ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ጋር ሊለዋወጥ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ለደንበኞቹም ሆነ ለባለድርሻ አካላት መረጃ የሚያስተላልፈበትና እራሱን የሚያስተዋውቅበት  ድረ-ገጽ ሊኖረው ይገባል፡፡

51. በአዲቱ ወቅት ድርጅቱ በአብዛኛው የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን ከዋናው መ/ቤት ጋር የሚያገናኝው የኮምፒውተር ኔትወርክ ዝርጋታ ማከናወኑ ታውቋል፡፡ ሆኖም በናሙና ከታዩት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የባህርዳር የኔትወርክ መስመሩ ያልተዘረጋ ሲሆን፣ በጅማ፣አዲስ አባባ፣ አሰላ እንዲሁም በናዝሬት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ኔትወርኩ ቢዘረጋም ከዋናው መ/ቤት ጋር የየእለቱን የገበያ ሁኔታ በመረጃ መረብ አማካኝነት እንደማይለዋወጡ  እና አገልግሎቱ ተግባራዊ እንዳልተደረገ ታውቋል፡፡

52. ድርጅቱ አጥንቶ ተግባራዊ ባደረገው አዲሱ የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ላይ በረዥም ጊዜ ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል የኤሌክትሮኒክስ ዘዴን በመጠቀም ሽያጭን

ማከናወን የሚል እቅድ ቢኖረውም ድርጅቱ የመሰረታዊ የስር ሂደት ለውጥ ጥናት ተግባራዊ ካደረገ ከ4 ዓመታት በኃላም ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪም አሁን ድርጅቱ እየተጠቀመበት ያለውን ስታቲክ ድረ ገጽ ወደ ዳይናሚክ አለመለወጡን ተገንዝበናል፡፡

53. ስለሁኔታው የድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በእራሱ ወጪ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹን ከዋናው መ/ቤት ጋር የማገናኘት ስራ ተጀምሯል፡፡ በዚህም መሰረት በሁሉም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የኔት ወርክ መሰመር ዝርጋታ ተሰርቶ ያለቀ ሲሆን አሁን የቀራቸው የደ/ማርቆስ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ብቻ መሆኑን፤ ለዚህም ምክንያቱ ስራው እንዲሰራ ለኢትዮ ቴሌኮም አሳውቀው የተጠየቁት ዋጋ ከፍተኛ በመሆኑ EVDO ለመጠቀም እንደ አማራጭ ሀሳብ መያዛቸውን፤ እንዲሁም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን በቁሳቁስ ለመደገፍ እንደ ድርጅቱ አቅም የሚሟላት ተግባር እየተሰራ መሆኑን፤ የ Hardware ብልሽት ሲያጋጥማቸው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ብልሽቱን በውጭ አካላት የሚያሰሩበት ሁኔታ መኖሩን ገልጸዋል፡፡ ኃላፊው ይህን ቢሉም የተዘረጋውን ኔትወርክ በመጠቀም የመረጃ ልውውጥ እንዳልጀመሩና የኤሌክትሮኒክስ ዘዴ በመጠቀም ሽያጭ ማከናወን እንዳልጀመሩ ታውቋል፡፡ ይህንንም በተመለከተ ለምን እንዳልጀመሩ ምላሽ አልሰጡም፡፡

54. ድርጅቱ ከፍተኛ ወጪ አውጥቶ የዘረጋውን የኔትወርክ መስመር ተግባራዊ አለማድረጉ መረጃዎችን በቀላሉ ዋናው መ/ቤት ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ጋር ለመለዋወጥም ሆነ ለደንበኞቹ አስፈላጊውን መረጃ በወቅቱ እንዳያቀርብ ያደርገዋል፡፡

### ለድርጅቱ ሰራተኞች እና ባለድርሻ አካላት የሚሰጠውን ሥልጠና በተመለከተ

55. የእህል አያያዝና የምርት ጥራትን በተመለከተ ለሚመለከታቸው የመሰሪያ ቤቱ ባለሞያዎችም ሆነ የእህል አቅራቢ ህብረት ስራ ማህበራት በየዓመቱ ስልጠና የሚያገኙበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

56. በኦዲቱ ወቅት ድርጅቱ በ2004 በጀት ዓመት ለ 240 ሰራተኞች ትምህርት እንዲከታተሉ ብር 89,900 ወጪ ለማድረግ እቅድ ተይዞ የነበረ ቢሆንም ለ13 ሰልጣኞች ብር 3,129 ክፍያ ፈጽሟል፡፡ ይህም አፈጻጸም በሰልጣኝ ብዛት ከእቅድ አንጻር 5 በመቶ በክፍያ አንጻር 3 በመቶ ነው፡፡ እንዲሁም ድርጅቱ ባዘጋጀው የ2001-2004 እስትራቴጂክ እቅድ ላይ የእህል አያያዝ እና የምርት ጥራትን በተመለከተ በየዓመቱ አንድ ስልጠና የመስጠት እቅድ ቢኖረውም ከ2002-2004 ዓ.ም ድረስ በ2004 ዓ.ም የእህል ጥራትና ቁጥጥር ህክምናና የመጋዘን አያያዝ እዲሁም በሰነዶች አያያዝና አጠቃቀም ዙሪያ ከአሥሩም ቅርንጫፍ የስራ ሂደቶችና ከእህል ግዥና ሽያጭ ወሳኝ የሥራ ሂደት የተወጣጡ ለ27

ሰልጣኞች ለ3 ቀናት ከተሰጠ ስልጠና ውጭ የተሰጠ ምንም ዓይነት ስልጠና አለመኖሩ ታውቋል፡፡

57. በዚህ ጉዳይ ላይ የድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ስልጠና በተለያየ ጊዜ የሚሰጡት አዲስ ለተመደቡት ሰራተኞች ብቻ መሆኑን፤በተለይ በእህል አያያዝና ክብካቤ ላይ ያሉአቸውን ሰራተኞች ከስራ ልምድ ብዛት ብቁ የሚሏቸው በመሆናቸው ሌሎች ክፍተቶች እየተለዩ ሥልጠና የሚሰጥበት ሁኔታ ለወደፊቱ እንደሚኖር ገልጸዋል፡፡

58. የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት ለሚመለከታቸው የድርጅቱ ባለሙያዎች፣ ለቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ባለሙያዎች እንዲሁም የእህል አቅራቢ ህብረት ስራ ማህበራት በቂ እና ተከታታይነት ያለው ስልጣናዎች አለመስጠቱ ድርጅቱ በሚያከናውነው የእህል ግዥ ጥራት፤ የእህል አያያዝ እና ክምችት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ይፈጥራል፡፡

**ከአምራቾችና ከሸማቾች ማህበራት ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተ፣**

59. ድርጅቱ የተለያዩ እህሎችን ለሽያጭ ከሚያቀርቡለት የተለያዩ የህበረት ሥራ ዩኒየኖች እና በየከተማው ገበያ ለማረጋጋት ከተቋቋሙ የሸማቾች ሕብረት ሥራ ማህበራት ጋር የስራ ግንኙነት የሚፈጥርበትን ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ ይህ ሥርዓትም በድርጅቱ የሚፈልገው እህል ተፈላጊውን ደረጃ አሟልተው ማቅረብ እንዲችሉ ለማህበራቱ የተለያየ ድጋፍ መስጠትን ሊያካትት ይገባል፡፡

60. ድርጅቱ በመሰረታዊ የስራ ሂደት ጥናቱ ላይ በእያንዳንዱ ከተማ እየተቋቋሙ ካሉ ዩኒየኖችን፣ የአምራቾችና የሸማቾች ሕብረት ሥራ ማህበራት ጠንካራና ጤናማ የስራ ግንኙነት የመፍጠር ተደራሽ ግብ ቢይዝም በመስክ የስራ ጉብኝት ወቅት በናሙና ተመርጠው ቃለመጠይቅ ከቀረበላቸው የህብረት ስራ ዩኒየኖች (ጋልማ ሁለገብ የገበሬዎች የህብረት ስራ ዩኒየን- አሰላ፤ ሊሙ አዳማ ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ስራ ዩኒየን- አዳማ ፤ ጅሬን የሸማቾች ህብረት ስራ ማህበር- ጅማ፤ እንዲሁም መርከብ ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ስራ ዩኒየን- ባህር ዳር) ለመረዳት እንደተቻለው ዩኒየኖች ከድርጅቱ ጋር ያላቸው የስራ ግንኙነት በእህል ህክምና እና በገበያ ማረጋጋት ስንዴ እህል ግዥ ብቻ የተወሰነ መሆኑ፤ ድርጅቱ ከዩኒየኖቹ የእህል ግዥ የማያከናውን መሆኑ እና የተለያዩ የምክር እና ስልጠና ድጋፍ ለዩኔየኖቹ የማይሰጥ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

61. በዚህ ጉዳይ ላይ የድርጅቱ የእህል ግዥ እና ሽያጭ ወሳኝ የስራ ሂደት ባለቤት ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በጥቅሉ አላማቸው የገበያ እድል የመፍጠር ሥራ መሆኑን፤ በራሳቸው እስከ ውጭ ኤክስፖርት ማድረግ እንደሚችሉ፤ እነሱ ግዥ ፈፀመው ወደ ሽያጭ ሲመጡ ዋጋቸው ከድርጅቱ የመግዣ ዋጋ ጋር ካልተመጣጠነ ግዥ እንደማይፈጽሙ በዋጋ

ከተስማሙ ግኘ፣ እንደሚፈጽሙ፤ ዋናው ነገር ገበሬው ያመረተውን ምርት የሚቀበለኝ/የሚረከበኝ አጣሁ የሚልበት ሁኔታ አለመፈጠሩ መሆኑን፤በአሁን ውቅት ድርጅታቸው የስንዴ ምርትን ከአምራቾች ለመግዛት በዝግጅት ላይ የሚገኝ መሆኑን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ኃላፊው ይህን ቢሉም በመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት ዕቅድ የተያዘውን ግብ ለምን ወደ ተግባር እንዳልተቀየረ እና እንዳላሳኩ ምላሽ አልሰጡበትም፡፡

## 2.4 የገበያ ማረጋጊያ ስንዴ እህል አቅርቦትና ስርጭትን በተመለከተ

62. በገበያ ላይ ያለውን የስንዴ ዋጋ ለማረጋጋት ድርጅቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የዋጋ ማረጋጋት ሥራን በጥናት ላይ የተመሰረተና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ ድርሻውን ሊወጣ ይገባል፡፡

63. ድርጅቱ መንግስት(የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር) የገበያ ዋጋን ለማረጋጋት ሲባል ከውጭ አገር ገዝቶ ወደ አገር ውስጥ የሚያስገባውን ስንዴ በመረከብ በየክልል በሚገኙ የድርጅቱ መጋዘኖች እና በዋናው መጋዘን ያከማቻል፡፡ ንግድ ሚኒስቴር በሚያዘጋጀው የስንዴና የዳቦ ስርጭት አፈጻጸም መመሪያ መሰረት የክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎች ለሚመርጧቸው የዱቄት ፋብሪካዎች፣ አከፋፋዮች፣ የሸማቾች ማህበራትና ዳቦ ቤቶች እንዲደርሳቸው በተወሰነው መጠን እና በተተመነው ዋጋ መሰረት የእጅ በእጅ ሽያጭ እንደሚያከናውን በኦዲቱ ወቅት ታወቋል፡፡ በኦዲቱ ወቅት የመስክ ጉብኝት በተደረገባቸው የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ሥር በሚገኙ መጋዘኖች ውስጥ ከባህር ዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በቀር ለዋጋ ማረጋጋት ሲባል ከውጭ አገር ተገዝቶ ለስርጭት የተዘጋጀ ስንዴ አለመኖሩን ተመልክቷል፡፡

64. የኦዲት ቡድኑ ከተለያዩ የሸማቾች ማህበራት፣ገበሬዎች ህብረት ስራ ዩኒየኖች እንዲሁም የዳቦና ዱቄት ማምረቻ ፋብሪካዎች በቃለመጠይቅ በሰበሰበው መረጃ በስንዴ ስርጭት ወቅት ንግድ ሚኒስቴር እና ንግድ ቢሮ በሚተምንላቸው ኮታ መሰረት ከኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት ያለምንም ችግር እየወሰዱ መሆናቸውን ገልጸውልናል፡፡ የኦዲት ቡድኑ ለመስክ ጉብኝት በተለያዩ የድርጅቱ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች በተዘዋወረበት ወቅት የማረጋጊያ ስንዴ በስፋት በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በሚገኙ መጋዘኖች ውስጥ ባለመኖሩ እና አየተከፋፈል በለመገኘቱ ህብረተሰቡ ከማረጋጊያው ስንዴ ምንያህል መጠቀሙን ለማወቅ አልተቻለም፡፡

# ክፍል ሦስት

# የመደምደሚያ ሃሳቦች

65. ድርጅቱ የእህል ግዥ እና ሽያጭ አፈጻጸም እና ክምችትን በተመለከተ ቀጥሎ የተመለከተቱት ችግሮች ያሉበት መሆኑ ታውቋል፡፡

- የድርጅቱ የየበጀት ዓመት የእቅድ ዝግጅት በተለይም የእህል ምርት ግምገማ መረጃ በበቂ ጥናት እና መረጃ ላይ ተመርኩዞ አለመሆኑ፣
- ድርጅቱ እህልን እንደ የጥራት ደረጃቸው ዋጋ በማለያየት መግዛት የሚያስችል ስርዓት በመዘርጋት የግዥ መጠንን ማሳደግ አለመቻሉ፣
- ድርጅቱ የየበጀት ዓመቱ የእህል ግዥ እና ሽያጭ ወሳኝ የስራ ሂደት በአብዛኛው የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚያከናውነው ስራ ከእቅድ በታች መሆኑ፣
- በድርጅቱ ተጠንቶ እና ጸድቆ ተግባራዊ በመደረግ ላይ ባለው የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት መሰረት በእህል ግዥ ወቅት የዋጋ የመወሰን ስልጣን በተወሰነ መልኩ ለቅርንጫፎች እንዲሁም ለወሳኝ ስራ ሂደት ባለቤቱ ያልተሰጠ መሆኑ፣
- ድርጅቱ የሚሳተፍባቸውን የእህል ንግድ ዓይነቶች በማሳደግ እና የገበያ እድልን በማስፋት የውጭ ንግድ ሽያጭ ድርሻውን ማስፋት አለመቻሉ፣
- ለእህል ግብይት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ለግዥ ጣቢያ ኃላፊዎች ለእህል ግብይት በየስማቸው ገንዘብ የሚላክ መሆኑና የሚላከው ገንዘብ በአግባቡ ሥራ ላይ ለመዋሉ ለመከታተል የሚያስችል የቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣
- በመጋዘን የሚቀመጡ እህሎች አቀማመጥና አደራደር የተዘበራረቀና ድርጅቱ ባስቀመጠው መመሪያ መሰረት አለመሆኑ፣
- ለእህል ህክምና ሚውሉ መድሃኒቶች ተዝረክርከው መቀመጣቸው እና የተበላሹ የእህል ማበጠሪያ ማሽኖች ከእህል ጋር ተደባልቀው በአንድ ላይ የተቀመጡ መሆኑን፣
- የእህል ጥራት እና ቁጥጥር ክብከቤ አፈጻጸም መመሪያ እና ሌሎች ተያያዥ መመሪያዎች ከመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ጋር በተዛመደ መልኩ ያልተከለሱ መሆኑ፣ ያሉትም መመሪያዎች በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ የማይገኙ መሆኑን፣
- ድርጅቱ በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚገዛቸው እና የሚያከማቻቸው እህሎች በድርጅቱ በተዘጋጀው የእህል ጥራት ቁጥጥር ክብካቤ እና ክምችት አስተዳደር መመሪያ መሰረት ተግባራዊ እየተደረገ አለመሆኑ፣
- ድርጅቱ የእህል ጥራት ቁጥጥር የሚያከናውንባቸው መሳሪያዎች በዘመናዊ መልኩ

ለመተካት በስትራቴጂክ ዕቅድ የተያዘ ቢሆንም አለመተካታቸው፣

- ድርጅቱ ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ጋር መረጃ ለመለዋወጥ የዘረጋው የኔትወርክ መስመር ሥራ ያልጀመረ መሆኑ፣ የኤሌክትሮኒክስ ሽያጭ ለመጀመር በዕቅድ ቢያዝም ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣
- ድርጅቱ በመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ላይ እንደ ባለድርሻ አካላት ከለያቸው መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር ያለውን የስራ ግንኙነት ለመፈጸም የዘረጋው ሥርዓት የሌለ መሆኑ፣
- ከሚመለከታቸው አካላት ጋርም በመቀናጀት ህገወጥ የእህል ንግድ ለመከላከል የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ያልሰራ መሆኑ፣
- በእህል ግዥ እና ሽያጭ ከተሰማሩት የተለያዩ የገበሬዎች ህብረት ስራ ዩኒየኖች እና ሸማቾች ማህበራት ጋር ያለው የስራ ግንኙነት በእቅድ በተደገፈ እና ወጥነት ባለው መልኩ አለመሆኑ፣
- ድርጅቱ ለሚመለከታቸው በድርጅቱ ዋና መስሪያ ቤትም ሆነ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ለሚገኙ ባለሞያዎች እንዲሁም የእህል አቅራቢ ህብረት ስራ ማህበራት ስለ እህል አያያዝ እና አጠባበቅ የተለያዩ ሙያዊ ስልጠናዎች በበቂ እና ተከታታይነት ባለው መልኩ እየሰጠ አለመሆኑ፣

66. በአጠቃላይ ድርጅቱ የእህል ግብይት አፈጻጸሙን በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ ዕቅድ እያቀደ ተግባራዊ ካላደረገ፣ የሚገዛውንና ለገበያ የሚያቀርበውን እህል ጥራትና ደረጃ የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ከልዘረጋ እና ዘመናዊና ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥና አያያዝ ሥርዓት ካልዘረጋና ተግባራዊነቱ የሚያረጋግጥ ጠንካራ የክትትል እና የቁጥጥር ሥርዓት ካከሌለው የተቋቋመበትን አላማ እንዳያሳካ የሚያደርገው እና የሚሰራው ሥራ ስኬታማነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድር መሆኑ ይታወቃል፡፡ ስለሆነም በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን የአሰራር ግድፈቶችና ድክመቶች ያሻሽላሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

# የማሻሻያ ሃሳቦች

- የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት በስሩ የሚተዳደሩትን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከየግብርና ጣቢያዎች የሚሰበስቡት የሰብል ግምገማ መረጃዎችን ወጥነት ባለውና በመረጃ በተደገፈ መልኩ እንዲሰበስቡ በማድረግ እንዲሁም የእህል ግዥን በእህል ጥራት ደረጃው በመከፋፈል ግዥ የሚፈጸምበትን ስርዓት በመቅረጽ በየበጀት ዓመቱ በጥናት ላይ የተመሰረተ ዕቅድ ሊይዝና በየበጀት ዓመቱ የሚገዛውን የእህል መጠን እና አይነት ሊያሳድግ ይገባል፡፡
- የእህል ግዥ እና ሽያጭ ዋጋ የመወሰን ስልጣን  የድርጅቱ የእህል ግዥ አፈጻጸም መመሪያን እና  የመሰረታዊ የአሰራር ስርዓት ለውጥ ጥናትን መሰረት በማድረግ እና በማጣጣም  ግልጽ የሆነ እና የእህል ግዥ እና ሽያጭ አፈጻጸምን ሊያጠናክር የሚችል የስልጣን ውክልና ሊሰጥ ይገባል፡፡
- ለእህል ግብይት ሲባል ለግዥ ማዕከላት ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በግለሰቦች ስም የሚላከው ገንዘብ በሚፈለገው ጊዜና ለተባለለት ዓላማ መዋሉን ለመከታተል የሚያስችል ወጥ የሆነ የቁጥጥር ሥርዓት ዘርግቶ ድርጅቱ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ድርጅቱ የሚሳተፍባቸውን የእህል ንግድ ዓይነቶች በማሳደግ እና የገበያ እድልን በማስፋት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸውን እህሎች በተጠናከረ እና ተከታታይነት ባለው መልኩ አለም አቀፉን የገበያን ሁኔታ በማጥናት እና ወደ ስራ ውስጥ በመግባት በአገር አቀፍ ደረጃ ያለውን የውጭ ንግድ ሽያጭ ድርሻውን ከፍ በማድረግ የተቋቋመበትን ዓላማ ሊያሳካ ይገባል፡፡
- የድርጅቱ የእህል ክምችት አያያዝና አጠባበቅን የተሻለ እና ውጤታማ ለማድረግ እንዲቻል ድርጅቱ መጋዘኖቹን በበቂ እና ዘመናዊ በሆኑ የእህል ጥራት ማረጋገጫ መሳሪያዎች ማጠናከር እንዲሁም በእህል ጥራት ቁጥጥር ስራ ላይ ለተሰማሩ ባለሞያዎች ወጥነት ያለውና ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ስልጠና መስጠት የሚቻልበትን ስርዓት ሊዘረጋና ለተግባራዊነቱ  አስፈላጊውን ቁጥጥርና ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የሚጠቀምባቸውን የአሰራር መመሪያዎች ከተጠናው መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ጋር በማጣጣም ሊከለሱና ወቅታዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡

- ድርጅቱ ዋናውን መ/ቤት ከቅርንጫፍ መ/ቤቶች ለማገናኘት እና በቀላሉ መረጃዎች ለመለዋወጥ በከፍተኛ ወጪ የዘረጋውን የኔትወርክ መስመር ዝርጋታ ተግባራዊ በማድረግ ዘመናዊ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓትን ሊያስጀምር ይገባል፡፡በተጨማሪም የዘረጋውን የመረጃ መረብ በማሻሻል በእቅድ እየተያዘ ተግባራዊ ያልተደረገውን የኤሌክትሮኒክስ ሽያጭ ሊጀምር ይገባል፡፡
- ድርጅቱ መንግስታዊም ሆኑ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የሥራ ግኝኙነቱን ሊያጠናክርና ህገወጥ የእህል ንግድ ለመከላከል የራሱን ድርሻ ሊወጣ ይገባል፡፡
- ገበሬው ለአመረተው እህል አግባብነት ያለው ክፍያ እንዲያገኝ እንዲሁም የሚያመርተው ምርት ጥራት ኖሮት ለአለም ገበያ እንዲቀርብ ድርጅቱ በእህል ጥራት አያያዝ ዙሪያም ሆነ በሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች በየክልሉ ከተመሰረቱ የገበሬዎች ህብረት ስራ ማህበራት እና ዩኒየኖች ጋር ተባብሮ የሚሰራበት ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

በአጠቃላይ ድርጅቱ የእህል ግብይት አፈጻጸሙን በበቂ ጥናት ላይ በመመስረት እቅድ ሊይዝ እና ተግባራዊ ሊያደርግ፣ የሚገዛውንና ለገበያ የሚያቀርበውን እህል ጥራትና ደረጃ የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ሊዘረጋ እና ዘመናዊና ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥና አያያዝ ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊነቱ የሚያረጋግጥ ጠንካራ የክትትል እና የቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ በማድረግ በማቋቋሚያ ደንብ የተሰጠውን ግዴታ መወጣት ይጠበቅበታል፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት፣ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹና በኦዲቱ ወቅት መረጃ የተሰበሰበባቸው የህብረት ሥራ ዩኒየኖች እና የሸማቾች ህብረት ሥራ ማህበራት ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

**አባሪ 1**

# የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

| *የኦዲት ጭብጥ* (audit Issue and sub issue) | *የመገምገሚያ መስፈርት* (Evaluative criteria) |
|---|---|
| 1. ***የእህል ግዥ እና ሽያጭ ክንውን እንዲሁም የእህል ክምችትና አያያዝ በብቃት እና ኢኮኖሚያው በሆነ መልኩ መከናወኑን መገምገም፡፡***<br><br>1.1 ***የእህል ግዥ እቅድ አፈጻጸም በተቀመጠለት የጥራት መጠንና አይነት መሰረት መከናወኑን መገምገም*** | 1. ድርጅቱ በእህል ግዥ እና ሽያጭ ላይ ደንበኛ ተኮር ቀልጣፋና ወጪ ቆጣቢ የሆነ አሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| | 2. ድርጅቱ በቅርንጫፍ ደረጃ የግገር እቅዱን አፈፃጸም ሊያሻሽል ይገባል፡፡ |
| | 3. በድርጅቱ የቅርንጫፍ ሰራተኞች እህልን መጋዘን ላይ ሲገዙ ድርጅቱ ባስቀመጠው የጥራት ደረጃ መመሪያ መሰረት ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | 4. ድርጅቱ የእህል ግዥን በመጠን፣ በአይነትና ፣በጥራት ማሳደግ ይኖርበታል፡፡ |
| | 5. በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ግዥ፣ሲከናወን የአፈጻጸም ስርዓቱን ሊያጠናክር የሚችል የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| 1.2 ***የእህል ሽያጭ እቅድ አፈጻጸም በተቀመጠለት የጥራት፤መጠንና አይነት መሰረት መከናወኑን መገምገም፡፡*** | 6. በእህል ሽያጭና ግብይት የስራ ሂደት ላይ የገበያ ጥናትና ልማት ውስንነት እንዳይኖር ድርጅቱ የስራ ክፍሎቹን በበቂ የሰው ኃይልና ቁሳቁሶች ሊያጠናክር ይገባል፡፡ |
| | 7. ድርጅቱ የቡና ኤክስፖርት እቅዱን በስትራቴጂክ ደረጃ ሲያዘጋጅ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ |
| | 8. የድርጅቱን ወቅታዊ የሆነ የእህል የገበያ ዋጋና ተዛማጅ መረጃዎች በድርጅቱ ድረ-ገጽ ሊኖር ይገባል፡፡ ምንጭ የእቅድና ገበያ ልማት ደጋፊ የስራ ሂደት ቢፒአር ገጽ 12 |
| | 9. ለእህል ጥራት ማረጋገጫ የሚውሉ የድርጅቱ መሳሪያዎች ዘመናዊና በበቂ መልኩ እና በሚፈለግበት የስራ ቦታዎች በበቂ ሁኔታ ሊሟሉ ይገባል፡፡ምንጭ የ2000-2004 እስትራቴጂክ እቅድ |
| | 10. የድርጀቱ የእህል ጥራት ቁጥጥርና ክምችት ክብካቤ የአፈጻጸም መመሪያ ከወቅቱ የድርጅቱ አደረጃጀትና የእህል ክብካቤ ሁኔታ ጋር በተጣጣመ መልኩ ሊከለስ እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| 1.3 ***የእህል ክምችትና አያያዝ ስርዓቱ በብቃት፤በጥራት እና ኢኮነሚያው በሆነ መልኩ መከናወኑን መገምገም፡፡*** | 11. የእህል ጥራትና ክብካቤ የሚደረግባቸው መሳሪያዎች በተገቢው የስነ ልክ ባለስልጣን የተፈተሹ መሆን አለባቸው፡፡ |
| | 12. የእህል አያያዝና የምርት ጥራትን በተመለከተ ለሚመለከታቸው የመሰሪያ ቤቱ ባለሞያዎችም ሆነ የእህል አቅራቢ ህብረት ስራ ማህበራት በየዓመቱ ስልጠና የሚያገኙበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡ |
| | 13. ድርጅቱ በየከተማው እየተቋቋሙ ካሉ የአምራቾችና የሸማቾች ሕ/ሥ/ማህበራት ጋር ጥብቅ የሆነ የስራ ግንኙነት የሚፈጥርበትን ሥርዓት ሊያመቻች ይገባል፡፡ምንጭ የእህል ግዥና ሽያጭ ቢፒአር ገጽ 9፡፡ |
| 2 ***የገበያ ማረጋጊያ ስንዴ እህል አቅርቦት በበቂ ጥናት በተደገፈ መልኩ መከናወኑን መገምገም፡፡*** | 14. ድርጅቱ ለገበያ ማረጋጋት አገልግሎት ላይ የሚውለውን ስንዴ ከውጪ ሀገር ከማስገባቱ በፊት ስለ እህል ጥራቱ አስፈላጊውን ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡ምንጭ መልካም ተሞክሮ |
| | 15. ድርጅቱ ከገበሬዎች እህል ከመግዛቱ በፊትም ሆነ ከውጭ ገበያ ወደ ኃገር ውስጥ የገበያ ማረጋጊያ እህል ከማስገባቱ በፊትየገበሬዎች እህል ለማምረት ያወጡት ወጪ ሀገር አቀፍ በሆነ መልኩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ሊያጠና ይገባል፡፡ምንጭ መልካም ተሞክሮ |